በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF URBAN DEVELOPMENT AND HOUSING

# የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ

URBAN LAND DEVELOPMENT AND MANAGMENT

## *የመሬት አቅርቦት፣ግብይትና አስተዳደር መምሪያ*

***ወደ ሊዝ የገቡ ከተሞች ለሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ድህረ-ገጽ አጠቃቀም ላይ ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የተሰጠ ግብረ-መልስ***

መጋቢት/2008

ከ/ል/ቤ/ሚ

## 1.መግቢያ

መንግስት የሀገሪቱን ከተሞች የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ስርዓቱን በማዘመን የኪራይ ሰብሳቢነትን ፖለቲካል ኢኮኖሚ በመናድ በምትኩ የልማታዊ ፖለቲካል ኢኮኖሚ ለማስፈን ትኩረት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴርም ዘርፉን ከኪራይ ሰብሳቢነት በማላቀቅ መሬት ለከተሞች ልማትና ለኢኮኖሚው እድገት የራሱን ሚና እንዲጫወት የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ስርዓቱን ማሳለጥ የሚያስችል ስትራቴጂ በመቅረፅ እና የማስፈፀሚያ የሊዝ አዋጅ በማዘጋጀት ለውጤታማነቱ ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህም በርካታ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡

የከተማ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ስራዎችን ስርዓት ለማስያዝ የወጣው የሊዝ አዋጅ 721/2004 ከተሞች የከተማ ቦታን በሊዝ ጨረታ እና በምደባ ብቻ እያቀረቡ ማስተላለፍ እንዳለባቸዉ በግልፅ ደንግጓል፡፡ በመደበኛ እና በልዩ የሊዝ ጨረታ ለተጠቃሚ የሚተላለፉ ቦታዎች ደግሞ ግልፅ የጨረታ ሂደትን መከተል እንደሚገባ ከአንቀፅ 8-11 ላይ በግልፅ ተመላክቷል፡፡በዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ለጨረታ የሚወጡ ቦታዎችን በአመታዊ እቅድ መያዝና ለከተማው ነዋሪ ይፋ ማድረግ፣በሁለተኛ ደረጃ በየጊዜው ቦታዎች ለጨረታ በሚቀርቡበት ወቅት በተለያዩ የህዝብ መገናኛ ብዙሀን ለሰፊው ህዝብ ተደራሽ በሚሆን አግባብ ማስታወቂያውን ማስተላለፍ እንደሚገባ እና በሶተኛ ደረጃ ደግሞ የጨረታ የአሸናፊዎች ዝርዝርና ያገኙት የውድድር ውጤት በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለህዝብ ይፋ መደረግ እንዳለበት በግልፅ ተቀምጧል፡፡

በከተሞች የሊዝ ጨረታን ማስታወቂያን በተለያዩ ሚዲያዎች እና ተደራሽ በሆኑ የህዝብ መገናኛ ብዙሀን ይፋ ባለመደረጋቸው የመልካም አስተዳደር እና የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ እየሆኑ መምጣታቸው በከፍተኛ አመራሩ መሪነት በተደረገው ጥናት ላይ በግልፅ ተመላክቷል፡፡ በመሆኑም የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ይህን የኪራይ ሰብሳቢነት ምንጭ ለማድረቅ በመልካም አስተዳደር እቅድ ተነድፎ እንዲሰራበት ከማድረጉ በተጨማሪ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የዕቅድ ዘመን ሁሉም ወደ ሊዝ የገቡ ከተሞች የጨረታ ማስተወቂያ እና ውጤታቸውን የክልሎችን የመገናኛ ሚዲያ ተቋማት መጠቀም እንደተጠበቀ ሁኖ በተጨማሪነት **የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ድህረ-ገፅ** በመጠቀም ማውጣት

እንዳለባቸው በእቅድ ተይዞ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ በዚህም የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ በየጊዜው ለጨረታ የሚያወጡ ከተሞችን እየተከታተለ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ እንዲጭኑ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ለሁም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የጨረታ ማስታወቂያ ቅፅ በማዘጋጀት ደብዳቤ እንዲደርሳቸው የተደረገ ሲሆን በመስክ ለ30 ከተሞች ክትትልና ድጋፍ በማድረግ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ድህረ-ገፅ እንዲጠቀሙ ግፊት ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት በየክለሉ ያሉት ከተሞች ያላቸውን ምላሽ እና ያሉበትን ደረጃ በሚተነትን መልኩ እንደሚከተለው ግብረ-መልስ ተዘጋጅቶ ተሰጥቷቸዋል፡፡

## 2. ወደ ሊዝ ስሪት የገቡ ከተሞች ላሏቸው ስድስት ክልሎች እና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች የተሰጠ ግብረ-መልስ

### 2.1.የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

በክልሉ 72 ወደ ሊዝ ስሪት የገቡ ከተሞች ያሉ ሲሆን ከሌላው ክልል በተለየ አግባብ በየጊዜው የከተማ ቦታን በሊዝ ጨረታ በተከታታይ በማዉጣት እየተላለፈ ሲሆን በአብዛኛው ከተሞች ለህዝብ ይፋ የሚደረገዉ የክልሉን የመገኛኛ ብዙሀን በመጠቀም ሲሆን በመስክ ክትትልና ድጋፍ በተደረገባቸው አንዳንድ ከተሞች (ኮረም፣ሽሬ እንዳባጉና እና አላማጣ) ደግሞ ጨረታዉ ለህዝብ ይፋ የሚደረገዉ የጨረታ ማስታወቂያ ሰሌዳን ብቻ በመጠቀም ብቻ እንደሆነ ታይቷል፡፡ በክልሉ በኩል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ የሊዝ ጨረታ የሚያወጡ ከተሞች እንዲጭኑ በተደጋጋሚ በደብዳቤ በተጠየቀው ጥያቄ እና በአካል በክትትልና ድጋፍ ግብረ-መልስ የተሰጠ ቢሆንም እስከ አሁን ከመቀሌ ከተማ አስተዳደር በስተቀር የጨረታ ማስታወቂያ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ አንድ ጊዜ ከተጫነው እና የ29 ከተሞች የሊዝ ጨረታ ዉጤት እንዲጫን ከመደረጉ በስተቀር በየጊዜው የሚወጣውን የጨረታ ማስታወቂያ አልተጫነም ፡፡ ይሁን እንጂ ከተለያየ አካላት እንደምንሰማዉ በክልሉ ያሉ በርካታ ከተሞች የሊዝ ጨረታ እያወጡ በክልል መገናኛ ብዙኃን ብቻ እንዲተላላፍ እያደረጉ እንደሆነ ቢታወቅም በሚ/ር መ/ቤታችን ድህረ-ገጽ ላይ ግን ማስጫን አልተቻለም፡፡

በዚህም ክልሉ የመሬት ሊዝ ጨረታን ለመላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ተደራሽ በማድረግ ረገድ ከሌሎቹ ክልሎችና ከተሞች አንጻር ሲነፃፀር እጅግ ወደኋላ የቀረ ነው ።

በመሆኑም የበላይ አመራሩ በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በየጊዜው ለጨረታ የሚቀርቡትን ከተሞች በማሳመን በወቅቱ ለክልሉ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ተቋም እንዲልኩ በማድረግ ወይም በቀታ ለሚኒስትር መስሪያ ቤቱ እንዲልኩ የቅርብ ክትትል  በማድረግ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ  በወቅቱ ተልኮ ለሰፊው ህዝብ ተደራሽ እንዲሆን ሚናቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 2.2.የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሰት በርካታ ወደ ሊዝ የገቡ ከተሞች (200) ያሉት ሲሆን እንደ ትግራይ ክልል ከተሞች ተከታታይነት ያለው የሊዝ ጨረታን እያወጡ ባይሆንም የተወሰኑ ከተሞች የከተማ ቦታን በሊዝ ጨረታ እያቀረቡ ለተጠቃሚ እያስተላለፉ እንደሚገኙ ይታወቃል፡፡ ከተሞቹ የጨረታ ማስታወቂያቸውን በአብዛኛው ለህዝብ ይፋ የሚያደርጉት የክልሉን የመገናኛ ብዙሀን በመጠቀም ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የክልሉ አንዳንድ ከተሞች( ከሚሴ፣ኮምቦልቻና ባቲ) የሚ/ር መ/ቤታችንን ድህረ-ገጽ መጠቀም መጀመራቸዉ አበረታች ተግባር ነዉ፡፡ በመስክ ክትትልና ድጋፍ ባደረግንባቸው ሁለት ከተሞች (ባህርዳር፣ ደብረ-ብርሃን፣ጫጫ እና ጎንደር) በወቅቱ የሊዝ ጨረታ ያላወጡ መሆኑን የተረዳን ሲሆን የመህልሜዳ እና ወገልጤና ከተሞች በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በተደረገው ክትትል እና ግንኙነት መረጃውን  እንዲልኩልን በማድረግ የሊዝ ጨረታ  ማስታወቂያቸውን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ እንዲጫን ተደርጓል፡፡ በክልሉ በኩል በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ ጨረታ የሚያወጡ ከተሞች እንዲጭኑ ሁለት ጊዜ  በደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን  በመስክ ክትትልና ድጋፍ የተሰጠውን  የአካል ግብረ-መልስ ወደ ጎን በመተው እስከ አሁን ከከሚሴ፣ባቲ እና ኮምቦልቻ ከተማ ዉጪ  ክክልሉም ሆነ ቀጥታ ከከተሞች የተላከ መረጃ  ባለመኖሩ የአብዛኞች  የክልሉ ከተሞች በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ እንዲጫን  አልተደረገም፡፡ ከዚህ ባሻገር የክልሉ መሬት ልማትና ማኔጅመንት የስራ ሂደት የተላከ የ34 ከተሞች የሊዝ ጨረታ ዉጤት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል  ላይ እንዲጫን ተደርጓል፡፡

በመሆኑም የክልሉ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ተቋም የመልካም አስተዳደር ችግር የምናስወግደበት እና የኪራይ ሰብሳቢነትን ሰንሰለት የምንዘጋበት አንዱና የመጀመሪያው ጉዳይ የጨረታ ማስታወቂያን ተገቢዉን ሚዲያ በመጠቀም ለህዝብ ተደራሽ  ስናደርግ እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ በዚህም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ መረጃውን  ለመጫን እንዲቻል የክልሉ ከተሞች የጨረታ ማስታወቂያቸውን ወቅቱን ጠብቀው እንዲልኩ የማሳመን  እና የቅርብ ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ክልሉ ሀላፊነቱን ሊወጣ ይገባዋል፡፡

## 3.3 የደቡብ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

የደቡብ ክልላዊ መንግስት በርካታ ወደ ሊዝ ስሪት የገቡ ከተሞች ያለው ሲሆን  ተከታታይነት ያለው ጨረታን እያወጡ ለህዝብ እያስታላለፉ ባይሆንም የተወሰኑ ከተሞች የከተማ ቦታን በሊዝ ጨረታ እያቀረቡ በማስተላላፍ ላይ እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከተሞቹ የጨረታ ማስታወቂያቸውን በአብዛኛው ለህዝብ ይፋ የሚያደርጉት የክልሉን የመገናኛ ብዙሀን በመጠቀም ነው፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የክልሉ አንዳንድ ከተሞች (ወልቂጤና ሐዋሳ) የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያዎችን በሚ/ር መ/ቤታችን ድህረ-ገጽ ላይ እንዲጫንላቸዉ አድርገዋል፡፡ ቡታጅራ እና ሚዛን ቴፒ ከተሞች የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያዎችን ከአዲስ ዘመን ጋዜጣና ከከተሞቹ ጋር በተደረገ የስልክ ልዉዉጥ የጨረታ ማስታወቂያዉ በሚ/ር መ/ቤቱ ድህረ-ገጽ ላይ እንዲጫን ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኞቹ የክልልሉ ከተሞች ማስታወቂያቸውን በሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ግፅ ላይ እንዲጭኑ በተደጋጋሚ በደብዳቤ የተጠየቀውን ጥያቄ  እና በመስክ ክትትልና ድጋፍ የተሰጠውን  የአካል ግብረ-መልስ ወደ ጎን በመተዉ በክልሉ የመገናኛ ብዙሃን ብቻ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ እያወጡ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የሊዝ የጨረታ ማስታወቂያን ለህዝብ ተደራሽ ልናድርግበት የምንችለውን መንገድ በመከተል በጨረታ ሂደት የሚከሰተውን የኪራይ ስብሳቢነት አስተሳሰብ እና ሰንሰለት መቁረጥ መቻል ይኖርብናል፡፡ በዚህ መሰረት የክልሉ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ተቋም ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በየጊዜው የሊዝ ጨረታ የሚቀርቡትን ከተሞች እየተከታተሉ መረጃውን በመሰብሰብ ወይም ከተሞች በቀጥታ እንዲልኩ

ግፊት በማድረግ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ እንዲጫን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 3.4 ኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሰት ምንም እንኳን ከ662 በላይ ከተሞች በክልሉ ያሉ ቢሆንም እስከ አሁን ወደ ሊዝ የገቡና ሊዝን ተግባራዊ እያደረጉ ያሉ ከተሞች 44 ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ከተሞች ተከታታይነት ያለው የሊዝ ጨረታን እያወጡ ለህዝብ እያስተላለፉ ባይሆንም የተወሰኑ ከተሞች የከተማ ቦታን በሊዝ ጨረታ በማቅረብ እያስተላለፉ ይገኛሉ፡፡ከተሞቹ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያቸውን በአብዛኛው ለህዝብ ይፋ የሚያደርጉት የክልሉን የመገኛኛ ብዙሀን እና አዲስ ዘመን ጋዜጣን በመጠቀም ነው፡፡ እስከ አሁን በ15 ከተሞች (አዳማ፣ፍቼ፣ሰንዳፋ፣ሞጆ፣ቢሾፍቱ፣ጫንጮ፣ዝዋይ፣አርሲነገሌ፣ነቀምት፣ጅማ፣አሰላ፣ሰንዳፋ፣ሙከጡሬ፣ዱከም እና ሱሉልታ) በተደረገው ክትትልና ድጋፍ ከአሰላ፣ጅማ፣ፊቼ እና ዱከም ከተማ በስተቀር ግልፅ የሊዝ ጨረታ ያወጡ ከተሞች የሌሉ ሲሆን በተጓዳኝ የአሰላ፣አጋሮ፣ጅማ፣ዱከም፣መቱ፣ጭሮ፣በደሌ እና የጎባ ከተማ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ የአዲስ ዘመን ጋዜጣን በመጠቀም ያወጡ ሲሆን በስልክ በመከታተል መረጃውን እንዲልኩ በማድረግ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ እንዲጫን ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአስራ አምስት ከተሞች የሊዝ ጨረታ ዉጤት ከክልል እንዲሰባሰብ በማድረግ በሚ/ር መ/ቤታችን ድህረ-ገጽ ላይ እንዲጫን ተደርጓል፡፡

በክልሉ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት አጀንሲ በኩል የከተሞችን የጨረታ መረጃ እየተከታተለ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ መላክ የሚጠበቅበት ቢሆንም እስከአሁን የአንድም ከተማ ሊልክልን አልቻለም፡፡ ፡፡ በሌላ በኩል ከተሞች የሊዝ ጨረታ ሲያወጡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል መጠቀም እንደሚገባቸው በተደጋጋሚ ለክልሉ በደብዳቤ የተጠየቀ ሲሆን በአካል ከተቋሙ ጋር በአስፈላጊነቱ ዙሪያ በተደጋጋሚ ውይይት ብናደርግም ለጉዳዩ ትኩረት ባለመስጠቱ ከተሞችን በማሳመን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ እንዲጫን ያደረጉት ጥረት የለም፡፡ በዚህም ክልሉ ከሌሎች ክልልችና ከተሞች አንጻር ሲታይ አፈጻጸሙ ዝቅተኛ ሆኖ ይገኛል፡፡ በመሆኑም የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያን ለሰፊው ህዝብ ተደራሽ ልናድርግበት የምንችለውን መንገድ በመከተል ለህዝብ ተደራሽ በማድረግ

በሊዝ ጨረታ ሂደት የሚከሰተውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት እና የኪራይ ሰብሳቢነትን ሰንሰለትን መስበር ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም በክልሉ የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ በኩል ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ከተሞችን በማሳመን በየጊዜው ለጨረታ የሚያቀርቡትን ከተሞች በወቅቱ እየተከታተሉ እና መረጃውን በመሰብሰብ ወይም ከተሞች በቀጥታ ለሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ ቀደም ብለው እንዲልኩ በማድረግ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ እና ፖርታል ላይ እንዲጫን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## 3.5.የቤንሻንጉል ጉምዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልላዊ መንግስት 10 ከተሞች ወደ ሊዝ የገቡ ሲሆን እሰከአሁን ባለው ሂደት አንድም ከተማ ግልፅ የሊዝ ጨረታ ያወጣ የለም፡፡ ይሁን እንጂ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ ቅፅ እና የሊዝ ጨረታ ሲያወጡ የሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱን ድህ-ገፅ እንዲጠቀሙ በተደጋጋሚ ደብዳቤ የደረሳቸው ሲሆን በመስክ ክትትልና ድጋፍም ከተሞች ጨረታ በሚያወጡበት ወቅት መረጃውን እንዲልኩ የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ይሁን እንጂ እስከ አሁን አንድም ከተማ ግልፅ ጨረታ በማውጣት ቦታ ማስተላለፍ ሲጠበቅባቸው ይህን ባለማድረጋቸው እንደ ድክመት የታየ ስለሆነ በቀጣይ በስፋት በግልፅ የሊዝ ጨረታ ቦታ እያወጡ ማስተላለፍ እንደሚጠባቸው አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

በመሆኑም ክልሉ ለከተሞች አስፋላጊውን ድጋፍ በማድረግ በስፋት ቦታ በማዘጋጀት በሊዝ ጨረታ እንዲያወጡ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡

## 3.6.ሐረር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት

ክልሉ አንድ ከተማ አስተዳደር ያለው ሲሆን እስከ አሁን ከተማው አንድም ቦታ በማዘጋጀት በሊዝ ጨረታ ያስተላለፈበት አግባብ የለም፡፡ ይሁን እንጂ የጨረታ ማስታወቂያ ቅፅ እና ከተማው የሊዝ ጨረታ ሲያወጣ የሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱን ድህ-ገፅ እንዲጠቀም በተደጋጋሚ ደብዳቤ የደረሳቸው ሲሆን በስልክ በተደረገው ክትትልና ድጋፍም ከተማው ጨረታ በሚያወጣበት ወቅት መረጃውን እንደሚልክ የጋራ ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡ይሁን እንጂ እስከ አሁን አንድም ጊዜ ግልፅ የሊዝ ጨረታ በማውጣት ቦታ ማስተላለፍ ሲጠበቅበት ይህን ባለማድረጉ እንደ ድክመት የታየ ስለሆነ በቀጣይ በስፋት በግልፅ ጨረታ ቦታ እያወጣ ማስተላለፍ እንደሚጠቅበት አቅጣጫ ተሰጥቷል፡፡

በመሆኑም ክልሉ ለሀረር ከተማ አስፋላጊውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በስፋት ቦታ አዘጋጅቶ ለተለያዩ አግልግሎቶች በገልፅ የሊዝ ጨረታ ማስተላለፍ ይጠበቅበታል፡፡

### 3.7.የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የሰጠውን አቅጣጫ በመቀበል በየጊዜው ለጨረታ የሚያወጣቸውን ቦታዎች ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ፣በከተማ አስተዳደሩ ድህረ-ገፅ ላይ ከማውጣት በተጨማሪ በተደረገለት የክትትልና ድጋፍ አግባብ በመጠቀም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ድህረ-ገፅ ተጠቅሞ የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያ ለህዝብ ይፋ እያደረገ መሬትን ለተጠቃሚ እያስተላለፈ ይገኛል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የጨረታ ውጤቱን ለሚኒስቴር መስሪያቤቱ በመላክም ይሁን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ እንዲወጣ በማድረግ መረጃውን ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ እና የሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮም መረጃውን በመውሰድ በድህረ-ገፅ ላይ እንዲጫን እያደረገ ይገኛል፡፡
በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ የሊዝ ጨረታን ማስታወቂያ እና የጨረታ ውጤቱን ለሰፊው ህዝብ ተደራሽ ለማድረግ የሚጠቀምበት አቅጣጫ ለሌሎች ክልሎችም አራያ ሊሆን የሚችል በመሆኑ ሌሎች ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የከተማ አስተዳደሩን መልካም ስራ በመከተል መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### 3.8.ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር

ከተማ አስተዳደሩ በዚህ በጀት አመት መጋቢት ወር መጨረሻ ላይ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚዉል ቦታ በማዘጋጀት የሊዝ ጨረታ አዉጥቶ እያስተላለፈ ይገኛል፡፡ በተደረገዉ ክትትልና ድጋፍ መሰረት የሊዝ ጨረታ ማስታወቂያዉን በከተማ አስተዳዳሩ ባሉ ሚዲያዎች፣አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ በኢትዮጵያ ብርድካስቲንግ ኮርፖሬሽን እና የሚ/ር መ/ቤታችንን ድህረ-ገጽ በመጠቀም ለህዝብ ይፋ ተደርጓል፡፡ በቀጣይም የጨረታ ዉጤቱን በተመሳሳይ ለህዝብ ይፋ እንደሚያደረግ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ ይሁን እንጂ ቦታ በስፋት በማዘጋጀት እና ወቅቱን ጠብቆ ጨረታ በማዉጣት ረገድ ሰፊ ዉስንንት ያለበት መሆኑ ታይቷል ፡፡

በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ በቀጣይ በስፋት ቦታ አዘጋጅቶ ለተለያዩ አግልግሎቶች በግልፅ የሊዝ ጨረታ በማውጣትና በማስተላለፍ የሊዝ አዋጁን በተግባር መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡

### 4.ማጠቃለያ

በስድስቱ ክልሎችና ሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች የሊዝ ጨረታ ማስታወቂና የጨረታ ውጤት የሚኒሰቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ግፅና ፖርታልን በመጠቀም ለህዝብ ተደራሽ ከማድረግ አንፃር በከተሞች በመስክ በተደረገው ክትትልና ድጋፍ እና በተጓዳኝ በተገኘው መረጃ መሰረት በዘርፉ የሚስተዋለውን የመልካም አስተዳደር እና የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር በመረዳት በአግባቡ ተግባራዊ እያደረገ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ሊመሰገን የሚገባው እና ሌሎችም የከተማ አስተዳደሩን አራያ ሊከተሉት ይገባል፡፡

የትግራይ ክልል ከተሞች የሊዝ ጨረታን በተከታታይ በማውጣት ለተጠቃሚ ማስተላለፋቸው በመልካም ጎን የሚፈረጅ ቢሆንም የጨረታ ማስታወቂያቸውን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ገፅ ላይ ባለመጫናቸው እና ለብዙሃኑ ህዝብ ተደራሽ ከማድረግ አኳያ ሰፊ ክፍተት ያለበት በመሆኑ በቀጣይ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት  መስራት ይጠበቅቸዋል፡፡ የአማራ፣ደቡብ እና ኦሮሚያ ክልል ከተሞች በተከታታይ የሊዝ ጨረታ በማውጣት ለተጠቃሚ በማታላለፍ ረገድ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተወሰኑ መሻሻሎች ቢኖሩም የሊዝ አዋጅ ከአስቀመጠው አቅጣጫ አንፃር ሲመዘን  እጅግ የሚቀራቸው መሆኑ ታይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ጨረታ የሚያወጡትን ከተሞች እየተከታተሉ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ድህረ-ግፅ ላይ እንዲጫን ከማድረግ አኳያም ሲመዘን  ጨረታ እያወጡ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱን ድህረ-ገፅ የማይጠቀሙ እንዳለ ተስተውሏል ፡፡ ስለሆነም ከተሞቹ በተከታታይ ጨረታ እንዲያወጡ እና  ማስታወቂያቸውንም በሚኒስቴር-መስሪያቤቱን ድህረ-ገፅ ላይ እንዲጭኑ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

በሌላ በኩል እስከ አሁን የሊዝ ጨረታ ያላወጡ ሐረረ ከተማ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ደግሞ የሊዝ አዋጁን ድንጋጌዎች በመከተል ከተሞች ጨረታ እንዲያወጡ በማድረግ መረጃው ለሰፊው ህዝብ ተደራሽ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡